ህዳር 16 ቀን 2002 ዓ.ም

# ከኢሕአፓ ምን እንማራለን!
# እስቲ ትንሽ ስለ ኢሕአፓ - ከአባይ ወንዝ በጭልፋ

ከአያልነሽ

ክፍል  ሁለት

**ኢሕአፓ፥ (የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ)**
**ልሣን ፥ ዴሞክራሲያ**
**ራዲዮ ፥ ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ  አንድነት ድምፅ**
**ደረ-ገፅ ፥ www.eprp.com**

ኢሕአፓ ይህን ያህል ፅናት ይዞ ለመቀጠል እንዴት ቻለ..? ለዚህ ጥንካሬውና አይበገሬነት አብነቱ ምንድር ነው ? ወዘተ.... ብዬ ነበር የክፍል አንድ ጽሁፌን ያቋረጥኩት። ለእነዚህና ለመሣል ጥያቄዎች የበኩሌንና የመሰለኝን በጥቂቱ ላካፍል ፈቀድኩና እነሆ! ክፍል 2ን ጀመርኩ።

በክፍል አንድ የመጀመሪያ ፅሁፌ ላይ ላስቀምጥ እንደሞከርኩት፣ ኢሕአፓ የተመሠረተው በኢትዮጵያ ሕዝብ መሠረታዊ ጥያቄዎች ጭብጥ ላይ ነው። እነኝህ መሠረታዊ ጥያቄዎች  ምን ምን ናቸው....? በውስጣቸውስ ምን ምን አካተዋል...?

**ሀ) የዴሞክራሲና ሠብዓዊ መብቶች ጥያቄ፥** ይህ ጥያቄ በውስጡ ዋና ዋና  የሆኑ መሠረታዊና ቁልፍ፣ቁልፍ ቁም ነገሮችን አጭቆ ይዟል።

- መደራጀት፣ የማንበብ፣ የመፃፍ፣ ኃሳብን በነፃ ያለ ተፅእኖ የመግለፅ፣ ከቦታ ቦታ የመዘዋወር/የመንቀሳቀስ ወዘተ.....

- ዜጎች በሐገራቸው በኢትዮጵያ እንደዜጋ እኩል የሚኖሩበት፣ ሐገሪቱ በከርሡ ምድሯ የያዘችውን እምቅ ሐብት ዜጋው በአግባቡና በእኩልነት እንዲጠቀምበትና እያንዳንዱም ዜጋ የባለቤትነት ስሜት ኖሮት፣ ሁሉም ዜጋ በጋራ የሚንከባከበው፣ እንደ ሐገር፣ የሐገራችን ኢትዮጵያ የጋራ ሐብትና የጋራ ቅርስ መሆኑን በመገንዘብ፣ የሚጠብቀው እንዲሆን....ወዘተ

- ዜጎች በሐገራቸው ጉዳይ ላይ የመወሰን፣ የመምረጥም ሆነ የመመረጠ ሙሉ መብትና እያንዳንዱ ደግሞ እኩል ድምፅና መብት እንዲኖረው ወዘተ......፣

- የትምሕርት ዕድል ለሁሉም ዜጋ እኩል እንዲዳረስ ወዘተ......

- ጤና አገልግሎት (ሕክምና) ዜጋው ሁሉም በአቅሙ እንዲያገኝ ወዘተ.....፣

- ዜጋው በቋንቋና በባህሉ ሳያፍር፣ ተከብሮና ባህሉም ሆነ ቋንቋውን ተጠብቆ እንዲኖር ወዘተ.....

**ለ ) የሥልጣን ባለቤትነት ጥያቄ፣** ማለትም

- ሕዝብ የሥልጣን ምንጭና የሥልጣኑ ባለቤት የመሆንና የማድረግ፣ ወዘተ....

## ሐ ) የሕግ የበላይነት ጥያቄ፥

- ማንኛውም ዜጋ/ሰው (የመንግሥት የበላይ አካል ነኝ፣ የጦሩ/የፖሊሱ አዛዥ ነኝ፣ የዚህ፣ የዚያ ባለሥልጣን ነኝ የሚል አካልንም ጨምሮ) ከሐገሪቱ ሕግ በላይ ሊሆን እንደማይችልና እንደማይገባ፤ በሌላ አባባል ማንኛውም ዜጋ በሕግ ፊት ዕኩል መሆኑና በሕግ እስካልተረጋገጠ ድረስም ወንጀለኛ ስለተባለ ብቻ፣ ወንጀለኛ እንዳልሆነና ሙሉ መብቱም የተከበረ ዜጋ መሆኑ፤ እያንዳንዱ ዜጋ ያለ ሕግ አላግባብ በተለይም በአመለካከቱ ወይም በአሰተሳሰቡ ሊታሠር፣ ሊገደል፣ ሊሰደድ፣ ሊጋዝ፣ ሊሰቃይ፣ የተለየ አመለካከት ስላለው/ስላላትና ስላቀነቀነ/ስላቀነቀነች የሐገሪቱን መተዳደሪያ ወይ ሕግ ወይም (ሕገ መንግሥት) ተገን አድርጎ አላግባብ ዜጋን ማስጨነቅና ማሳደድ ወዘተ... እንዳይኖር የሚሉት

የጥያቄዎቹ አንኳር መልዕክቶች ናቸው።

የተከበራችሁ አንባቢዎች ሆይ!

እነኝህ ከፍ ብለው በቅደም ተከተል የተቀመጡ አብይና ቁልፍ ጥያቄዎች ባለቤት፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ነው። በዚህ ጥያቄ ላይ ደግሞ አይከፍሉ መስዋዕትነትን የከፈለው በቅድሚያ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። ከመቼ ጀምሮ.....?

ዛሬ "**<u>ሥልጡን</u>**" ፖለቲከኞች ነን የሚሉትና በተደጋጋሚም በአፋቸው የ"21ኛው" ክህለ ዘመን ሰዎች ነን ማለትን የሚያዘወትሩ የፓል ቶክ አበጋዞች እንደሚያጫወቱን፣ ይህ ትግል ከዛሬ 18 ዓመት በፊት የተጀመረ ጥያቄና ትግል አይደለም/አልነበረም። በሀገራችን ዜጋው በከፋው ጊዜ በነጠላም ይሁን በቡድን እየሸፈተ መንግሥትን በማስጨነቀ፣ የሚጠይቀውን ለማግኘት የተከፋበትን ለመግለጽ በየወቅቱ ሞክሯል። በዚህ ጥያቄ ዙሪያ ምናልባት መልክ ባለውና በተደራጀ መንገድ ተጋድሎ ማድረግ የተጀመረው ግን ከግማሽ ምዕት ዓመት በላይ እንደሚሆነው የሚታወቅ ነው። ይህንን የሕዝብ ተጋድሎና የህዝብ መሠረታዊ ጥያቄ ብዙዎቹ በተለይም "ምሁሩ" እና ዛሬ ደግሞ በየፖለቲካ ድርጅቱ ውስጥ ገብተው "**በመሪነት**" ስማቸው ጎልቶ የሚጠራና እንዲጠራ የሚፈልጉ ግለሰቦች፣ እነኝህን ጥያቄዎች ከአንድ ድርጅት ጋር ብቻ በማያያዝ ያን ድርጅት አጠቃን ብለው፣ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ሁሌ ፊት ለፊት ሲላተሙ ይሰተዋላሉ። ይህ እንግዲህ የሚያመላክተው አሁንም ቢሆን እነኝህ ግለሰቦች ሆኑ ኃይሎች "**<u>በዴሞክራሲያዊ መብቶች</u>**" ጥያቄ ዙሪያ ላይ ያላቸውን የተዛባ ዕይታና፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ለእነዚህ መሠረታዊ መብቶች ያደረገውን ተጋድሎ፣ የከፈለውንም መስዋዕትነት እንደዘነጉት አመላካች ነው። ለዚህም ነው ሥልጣን ላይ የወጡትና የሚወጡት እብሪተኞችም ጭምር ቢሆኑ፣ ከእነኝህ የሕዝብ መሠረታዊ ጥያቄዎች ባፈነገጡ ቁጥር፣ በመሣሪያ/ጠብመንጃው አጥር ውስጥ ይከለሉና፣ ሕዝብን በጠመንጃቸው ጫፍ አጮልቀው አዘቅዝቀው ሲያዩት፣ ኢምንት መስሎ የሚታያቸው። ግብዞች ናቸውና እራሳቸውንም አግዝፈው ይመለከታሉ። እናም ሕዝብና እነርሱ ማዶ ለማዶ በዓይን ጫፍ እየተያዩ ለመዝለቃቸው እነሆ ዛሬም ድረስ እየተመለከትን ነው። ብዙ ዘመን!

በአንፃሩም በተቃዋሚ ሥም "**<u>ለመሠረታዊ ዴሞክራሲያዊ መብቶች</u>**" እሴት ነው የምንታገል ይሉና፣ የሕዝብንና የሐገርን ወርድና ስፋት በእነርሱ የጠበበ ዕይታ ሚዛን ውስጥ አስገብተው "**ይህን ያህል፣ ያን ያህል አባል አለን**" በሚል አባዜ፣ ብርቱውን የሕዝብ ኃይልና ዋናውን የሕዝብ ጥያቄ የተቀመጠበት ይጠፋባቸዋል። ታዲያ ይሄንን የሕዝብ ንብረት በአፍ ብቻ በመደግጋም በተግባራቸው ግን ከጀርባቸው የሚያሽከረክሩት የሕዝብ ጥያቄ፣ ሁሌም

ሊደፈጥቱት ሲሞክሩ እፊታቸው/ግንባራቸው ላይ መጥቶ እየተደፋ አላራምድ፣ አላንቀሳቅስ፣ አላላውስ ብሏቸው፣ ሲያሻው ሲበትናቸው፣ ሲያሻው ደግሞ አፈራርሶ ሲገጥማቸው..... ሲበቃው ደግሞ እንደ ሸከላ በታትኖ እርቃናቸውን አስቀርቷቸዋል፤ የሕዝብን መሠረታዊ ጥያቄ እንዳልሰሙና እንዳላዩ አድርጎ ማለፍ አይቻልምና። ለዚህ ሁሉ መሰናክልና እንቅፋት የሚዳርጋቸውን ጉልህ ችግር ማየት ይሳናቸውናም፣ ለውድቀታቸው ሁሉ ማጠየቂያ በመከረኛው ድርጅት ኢሕአፓ ላይ ይወረወራል። የሚገርመው ኢሕአፓ ባይኖርስ በማን እናሳበብ ነበር..? ብለው አለመጠየቃቸው ነው። ጎበዝ! አንዳንዴም እኮ የኢሕአፓ መኖር ለእነርሱም እንደሚጠቅማቸው ባይዘንጉት ምንኛ ማለፊያ በሆነ ነበር!

በመሠረቱ ኢሕአፓ እስከአሁን ለ35 ዓመት በፅናትና በአይበገሬነት ለመቀጠሉ አብነቱ፤ በእነኝህ የሕዝብ መሠረታዊ ጥያቄዎች ዙሪያ፣ ከቀን 1 ጀምሮ ለ35 ዓመት ሳያሰልስ ይዞ በማስተጋባትና፣ ከማንም ጋር ሳይደራደርባቸው፤ እንዲያውም ከምንም በላይ አጉልቶና አግዝፎ በሕዝቡም ውስጥ አርዓያ ሁኖ በመቀጠሉ ሕዝባችንም የኔ ብሎ ይዟቸው እንዲተም ማድረግ መቻሉ ነው። ወገኖቼ! ለኢሕአፓ ትልቁ ድል ይሄ ነው። ለኢሕአፓ ትልልቅ "**<u>ሥልጣኑ</u>**" እነኝህ ናቸው። የኢሕአፓ ጥንካሬ የሚለካውም እስከዛሬ ድረስ ለ35 ዓመት ማንኛውንም ዓይነት ከየአቅጣጫው (ከባእዳንም) ጭምር ለተወረወረበተ ቀስት ሆነ ሰይፍ፣ እንዲሁም ሕልውናውንም ጭምር ለማጠፋት የተደረገውን መረባረብ ተቋቁሞ የቀጠለበት ምስጢር፣ ስውር አይደለም። የኢትዮጵያን ሕዝብ ከጀርባው ስለያዘና ሁሌም ደጀንና ከንዱ ስለአደረገው ለመሆኑ፣ ጥርጣሬ ሊገባን አይገባም። የኢሕአፓ ሀብቱ ሕዝባዊነቱ ነው። የኢሕአፓ ሐብቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። ኢሕአፓ ትግል የሚያቆመው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ያቆመ እንደሆነ ነው።

ግፍ፣ ጭቆና፣ ዘረኝነት፣ ረኃብን ቀፍቃፊ ፈንጣዎች እስካሉ ጊዜ ደግሞ፣ ፈንጣውን ማጥፋት የግድ ነው! ፈንጣው የሚፈለፈልበትንም ጉድጓድ መድፈንና ማደረቅ ተገቢ ነው እንጂ፣ ሰው የሚበላው አጥቶ እየረገፈ ባለባት ኢትዮጵያ ውስጥ፣ ትግልን "**<u>በጊዜ ማሳለፊያነትና</u> <u>እንዲያው ዝም ብለን ለመቃውም</u>**" ወይንም "<u>ትግልን እንደሥራ ቆጥረን</u>" ሃ! ሃ! ሃ! ሃ! የተያዘ ነው ተብሎ መነገሩ፣ በጣም ያስቆጫል፤ ያሳዝናልም። ያውም እያስራቡ ቀጥቅጠው ለመግዛት የሚያስቡ ከፋ ባላንጣ ይዘን እያለ፣ ትግል "እንደሥራ" ተቆጥሮም ሥርዬት የሚገኝበት ከሆነም ቢከፈል፣ ይህንን የሚያስብል ባልሆነና ባልተገባ ነበር። የሆኖ ሆኖ ግን የችግራችን ሁሉ ዋና ጦስ፣ የተያያዝነው ትግል የምርና የሰው ሕይወትም እየተቀጠፈበት ያለ ለመሆኑ፣ ለአፍታም መዘንጋትችን ነው። የቅርቡን እንኳ ብንዘከር እነ ሽብሬ ደሰላኝ፣ ተጫውተውና ሮጠው ስይጠግቡ ፣ በጥይት ጭንቅላታቸው ተብርቅሶ መቀጠፋቸውን መርሳታችን እግዚኦ! የሚያሰኝ ነው።

ኢሕአፓ የተገነባው ከህዝብ ውስጥ ከታች ወደላይ እንጂ ከላይ ወደታች አይደለም። ለዚህም ነው የኢሕአፓ ሥጋና ደም የተሠራው ከታች ወደ ላይ በሕዝብ ልጆች የመስዋእትነት ድልዳል ነው የምንለው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለእነኝህ መሠረታዊ የመብት ጥያቄዎች ሲታገል ደግሞ ተደራጅቶ ነው። እንዴት ተደራጀ....?

ከዛሬ 40 ዓመት በፊት ለእነኝህ መሠረታዊ ለሆኑ የዴሞክራሲ መብቶች ሲታገል፣ የመታገያ ሕዝባዊ መሣሪያዎችን/ተቋሞችን ባሉበት አካል ሁኖ፤ በደከሙበት አጠናክሮና፣ በሌሉበት ደግሞ በራሱ ትግል አቋቁሞ ነው። ለምሳሌ፥

- የሠራተኛው ማህበር፣ የመምህራን ማህበር፣ የተማሪዎች ማህበር፣ የሴቶች ማህበር ወዘተ....የተባሉት ተቋሞች ዋና ዋና መሣሪያዎቹ ነበሩ።

- ሠራተኛው ጥያቄውን ለማስፈጸም ሲሻ/ሲፈልግ በዚሁ በማህበሩ አማካይነት ነበር የሚያቀርበው፤ ከመንግሥት ጋርም ሲደራደር በዚሁ በማህበሩ አማካኝነት ነበር።
- አስተማሪውም መሠረታዊ የሆኑ ጥያቄዎቹን የሚጠይቀው በመምህራን ማህበር አማካይነት ነበር። ከመንግሥት ጋር ተቀምጦ ሲደራደርም በዚሁ በማህበሩ አማካይነት ነበር። ወዘተ.....
- ተማሪውም እንዲሁ የራሱ ማህበር ስለነበረው በማህበሩ፣ በተማሪው ማህበር አማካይነት ...ወዘተ.... ማለት ነው።

ዛሬ፣ ዛሬ ታዲያ እነኝህ ከላይ የተዘረዘሩት ተቋሞች፣ ብርቱ መሣሪያ/ተቋም ሆነው እንዳገለገሉ ተዘንግቶ፣ ጭራሽ ዛሬ ደግሞ የተደራጁ ድርጅቶችን ጭምር **"ድርጅት"** አያሰፈልግም በሚል የተሳሳተ ብዥታ ውስጥ በመግባት፣ ያሉ ድርጅቶችን እንዲከስሙ መረባረብ፣ ምንኛ የሕዝባችንን ትግል የፉቅቅ እያስኬደው ለመሆኑ፣ መገመት አያዳግትም። የተደራጀና፣ ሌት ተቀን ኢትዮጵያን ለማጥፋት ይሁነኝ ብሎ ሳይታክት የሚሠራ ፀረ ኢትዮጵያ የሆነ ጠላት አስቀምጠን፣ እንዲህ ዓይነቱን ፀረ ኢትዮጵያ ኃይልን፣ ያለ ድርጅትና ያለ ተቋም ታግሎ ለውጤት ይደረሳል ማለት ቢያንስ የዋህነት ነው። የመደራጀትን ጥቅም እስከዛሬም አልመገንዘብ ደግሞ... መቼም **"እወቅ ያለው በ40 ቀኑ ያውቃል፣ አታውቅ ያለው ደግሞ በ40 ዓመቱም አያውቅ"** በሚል ማለፉን መርጫለሁ።

ውድ አንባቢዎች

**አስታውሱ!** በእነኝህ ተቋማት ውስጥ በእያንዳንዱ ማህበር ቢያንስ በሥራቸው ከ10 ሽህዎች በላይ አባሎችን ያስተናግዱ ነበር። እነኝህን ተቋሞች ደግሞ ህዝብ ያገኛቸው በችሮታ ሳይሆን፣ በከባድና እልህ አስጨራሽ በሆነ ትግል ነው። ኢሕአፓም በእነኝህ ተቋሞች ውስጥ ገብቶ ሲታገልና ሲያታግል እንደነበር፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ድብቅ አይደለም። በዚህ ትግል ውስጥ መስዋዕትነትን የከፈሉትም አያሌና የትዬለሌ ናቸው። ይህ ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝብ ተጋድሎ ነበርና የኢትዮጵያ ሕዝብም የሚያውቀው፣ አብሮም የተሠዋለት ነው። ለዚህም ነው ኢሕአፓ "የለም" ወይም "ጠፍቷል" ማለት የሚዳዳቸው ኃይሎች የሚዘነጉትና ማወቅም ያለባቸው፣ ኢሕአፓ የሚጠፋው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሌለ ብቻ ነው። ኢሕአፓ እንደ ድርጅት የተገነባው ደግሞ ከታች ወደላይ ነው ስንል በአጠቃላይ በእነኝህ ማህበራት ውስጥ ገብቶ ሲታገልና ሲያታግል ለመቆየቱ፣ ለአብነት ያህል በቅርቡ በመስዋዕትነት የተለዬንን ጓድ ሣሙዔል አለማየሁን ማንሣት ይቻላል። በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብት ተሟጓች እና የነፃ ጋዜጣ አዘጋጅ የነበረው ጓድ ተስፋዬ ታደሰም፣ እንዲሁ በ1985/86 ዓ.ም በወያኔ ጥይት ተደብድቦ አዲስ አበባ ላይ መሥዋዕት መሆኑ አይዘነጋም። በወያኔ ተይዛ ደብዛዋ እስካሁን የጠፋው ጓዳችን አበራሽ በርታም፣ ኢትዮጵያ ውስጥ በሴቶች ማህበርና በሠራተኛው ማህበር ውስጥ የጎላ ሚና እንደነበራትና፣ የነበራቸው ናቸው። ብዙዎችንም መጥቀስ ይቻላል - እነ ዳሮ ነጋሽም በዚሁ ተጋድሎ ህይወት የከፈሉ ናቸው ፤ እነ ማርቆስ ሐጎስን የመሣሠሉ ሁሉ የዚሁ የሠራተኛ ማህበር መሪ የነበሩና መስዋዕትነትም የከፈሉት ለዚሁ ማህበራቸውና መብታቸው ሲሉ ነው። ሌሎችም በሕይወት የሌሉና አሁንም በሕይወት ያሉ፣ እስከአሁንም በኢህአፓ ውስጥ በፅናት የሚታገሉ እንዳሉም መታወቅ አለበት።

በክፍል አንድ ፅሁፍ ላይ እንደገለጽኩት ኢሕአፓ በታሪኩ በአንድ ግለሰብ ተመርቶ አያውቅም። ኢሕአፓ አንድ መሪም የለውም። ኢሕአፓ የሚመራው በአባላቱ ነው። ኢሕአፓ ፕሮግራሙን የሚነድፈው በመላው አባላቱ ነው። ኢሕአፓዎች የድርጅታቸውን አመራር ከታች እስከ ላይ ያሉትን የሚመርጧቸውና የሚያወርዷቸው አባላት ናቸው። ኢሕአፓ የራሱ የሆነ የፓርቲ ልሣን አለው። ኢሕአፓ ሲመሠረት ጀምሮ **ዴሞክራሲያ** የሚባለውን ልሣኑን ይጠቀማል። እስከዛሬም የሚጠቀምበት ይሄንኑ ነው።

ኢሕአፓ ወቅታዊ በሆኑ ሐገራዊና ዓለም ዓቀፋዊ ሁኔታዎች በሚከሰቱበት ጊዜ ወዲያውኑ የ**ኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ ፓርቲ** (ኢሕአፓ) ብሎ **መግለጫ** ያውጣል። እነኝህ በየጊዜው የሚያወጣቸው **መግለጫዎች** የኢሕፓን አቋም የሚያንፀባርቁ ናቸው። እያንዳንዱን የኢሕአፓ አባልም የሚወክለው ይህ መግለጫ ነው። ልብ-በሉ! - እያንዳንዱ የኢሕአፓ አባል የሚወከለው በኢሕአፓ ይፋ **መግለጫ**ና በልሳኑ **ዴሞክራሲያ** በሚያቀርብው አቋሙ ብቻ ነው። በአንጻሩም ኢሕአፓ ውስጥ ያሉ አባሎች እንደ ዜጋም ነፃ የሆነ፣ የራሰቸው አስተሳሰብም ያላቸው እንደሆኑ መዘንጋት የለበትም። እያንዳንዱም የራሱን ነፃ አስተሳሰብ በማንኛውም ነገር መሰጠት የሚችልና መብቱ መሆኑንም ያውቃል።ነፃ ኃሳብ፣ ነፃ የፈጠራ ሥራ፣ ነፃ ተነሳሽነት፣ ነፃ ትችት......ወዘተ ለኢሕአፓዎች እንግዳ አይደሉም፣ ኢሕፓዎች እነኝህን ትውፊቶች ድሮ፣ ድሮ ነው በተግባር እየጠተቀሙ፣ እየፈተኑ ያለፏባቸው ድሮ! ድሮ። በትግሉ ዓለም ውስጥ ገብተው መታገል ከጀመሩበት ወቅት ጀምሮ ማለት ነው። ነፃ ኃሳብና አስተሳሰብ ደግሞ፣ የእያንዳንዱ ሰው የተፈጥሮ መብቱ ነው። ለእያንዳንዱ ደግሞ ይህንን መብት ማንም ሊንፍገው፣ ሊሰጠው የሚችል የለም። የእያንዳንዱ የራሱ ኃብት ነው። ይሄ መሰመር ያለበት አብይ ጉዳይ ነው። ዛሬ! ዛሬ በ40 ዓመት ያውም ስለ "ሠላምና ሠላማዊ ትግል" ስለ "ዴሞክራሲያዊ መብት" ትግል እያደረግን ነው ከሚሉ ኃይሎች፣ ለምን ይሄ ተፃፈ....? ለምን ያ ተተቼ? ለምንስ ትችት ይበዛል? ለሚሉ ግለሰቦች ሆኑ ኃይሎች ማለት የሚቻለው፣ አንድ ነገር ብቻ ነው። "**በነፃ የማሰብና የመፃፍ መብት**" አንዱ መሠረታዊ የዴሞክራሲ ሀ ሁ፣መሆነን ሁላችነም ልንገነዘብ ይገባል የሚል ነው።

ኢሕአፓ ይሄንን መሰል አትፃፉ፣ አትናገሩ፣ ዝም እንበል፣ ዝም ብሉ ከሚል አስተሳሰብ ጋር የተቆራረጠው፣ ገና ድሮ በ1967 ዓ.ም በይፋ ራሱን ኢሕአፓ ብሎ ከወጣ ጀምሮ ነው።... ያኔም ቢሆን ግን በመጻፉና...በመተቸቱ ነው ያ ሁሉ ሞት፣ ጭፍጨፋ፣እሥራት፣ እንግለትና የመሣሰሉት የደረሱበትና ለዚህም ዴሞክራሲያዊ አሴት ደግሞ ከሕዝብ ጋር ሆኖ የሕይወት መስዋዕትነት የከፈለበት። ስለዚህ ዛሬ ተመልሠን ከ40 ዓመት በኋላ ወደ ኋላ ልንመለስ ወይም ሊንሄድ አይጠበቅም። እንዲያውም እንዲህ ዓይነት ነገሮች፣ እንዲያደጉ፣ እንዲለመለሙ.... ሥር እንዲሰዱ፣ እንዲፋፉም፥ ኢሕአፓ ......ውኃ ያጠጣል እንጂ! ዛሬ በወያኔ የተዘጉት ኢትዮጵያ ውስጥ ይታተሙ የነበሩ የነፃ ጋዜጦችና መፅሔቶች ተግባራቸው፣ ይሄ ነበር። በመፃፍ ህዝበ ማወቅ ያለብትን ማሳወቅ፤ ህዝብ የማወቅ መብት አለውና። ስለዚህ እንዲያዉም ሁላችንም ነፃ ጋዜጦቻችን የታሠረቡት ሠንሰለት ይፈታ! ብለን መጮህ ይጠበቅብናል። እንዲያውም የታገዱበት "ሕገ ወያኔ" ይነሳላቸውና ሥራቸውን ይጀምሩ ብለን ሁላችንም ማስተጋባት ይኖርብናል እንጅ።

ኢሕአፓን ዛሬ በየአቅጣጫው የሚኮንኑት ኃይሎች ያልገባቸው፣ ድርጅታችን ኢሕአፓ እስከዛሬ በፅናት ለመቀጠሉ ዋና አብይ ጉዳይና ምስጢሩ፣ እንደ እነርሱ "አንድ ቆራጥ አብዮታዊ ወይም የቁርጥ ቀን መሪ " የሚባል ባለማስቀመጡ፣ ባለመጥረቡና፣ ባለመሾሙ ነው። በመሠረቱ ይህ አመለካከት በራሱ የተሳሳተ ነው። እንጂማ እነተስፋዬ ደብሳይን፣ ገለብ ዳፍላን፣ እነ ፀጋዬ ገ/መድህንን፣ እነስጦታው ሁሴንን፣ እነ ሣሙዔል አለማየሁን፣ እነ በለጠ አምኃን፣ እነጋይም ገ/ሚካኤልን፣ እነ ዮሴፍ አዳነን...ወዘተ፣...ወዘተ በርካቶች ሁሉም (የከፍተኛ አመራራ ኮሚቴ አባል የነበሩ) ናቸው ሲሰውብንና ተጠልፈው ደብዛቸው ሲጠፋብን፣ ትግሉ ይቆም ነበር። ነገር ግን ኢሕአፓ የተቋቋመበት ዋናው የመሠረት ድንጋይ፣ የሕዝብ መሠረታዊ ጥያቄዎች መልስ ያገኙ ዘንድ በመሆኑና ለዚህም ዕውን መሆን በኢሕአፓ ውስጥ ያሉ አባሎች በፈቃዳቸው የተሠለፉና ከተራ አባል ጀምሮ እስከ ከፍተኛው አመራር አባል ድረስ ያሉትም፣ ለዚህ ቅዱስ ዓላማ እስከ መጨረሻው ለመሠዋት ቃል የገቡበት በመሆኑ ነው። እያንዳንዱ የኢሕአፓ አባልም ለራሱ የውዴታ ግዴታ ቃል በመግባቱ ነው - በሙሉ ፈቃደኝነት።... ስለዚህም ነው ኢሕአፓዎች ኢትዮጵያ ውሰጥ በፓለቲካ አስተሳሰቡ ብቻ፣ ማንም ሰው እንኳንስ መገደል አንደም ሰው ቢሆን መታሠረ የለበትም የምንለው። ስለ ዴሞክራሲና ስለ ሠብዓአዊ መብት እታገላለሁ የሚል

ማንኛውም ኃይል ደግሞ፣ ይህንን ለማለት  ካልደፈረና ለመታገል ካልሞከረ ጥያቄ ውስጥ መግባቱ አይቀሬ ነው። ኢሕአፓዎች በዚህ መሰሶ ላይ ስልቆምን ነው ይኸው እስከዛሬ ድረስ በፅናት ለመታገል የበቃነው.....። ኢሕአፓ ሙሉ ነፃነት የሚሰማው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ፣ ነፃና ያልተሸራረፉ መብቶች ባለቤት ሲሆን ነው። ደግሞም የፈጀውን ያህል ይፍጅ እንጂ  ኢሕአፓ ትግል የሚያቆመው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ሲያቆመ ብቻ ነው።
ኢሕአፓ፣ በሕዝብ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ከሕዝብ ጀረባ ሊደራደር አይችልምም። ለምን...? እነኝህ ከላይ በቅደም ተከተል የዘረዘርኳቸው የሕዝብ መሠረታዊ መብት ጥያቄዎች ባለቤት፣ ማንኛውም የፖለቲካ ድርጀት አይደለም። የእነኝህ ጥያቄዎች ባለቤት የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። በመሆኑም ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት በእነኝህ የህዝብ ንብረቶች ላይ ከህዝብ ጀርባ ሊደራደርባቸውም አይፈቀድለትም ማለት ነው። ቢያንስ ኢሕአፓ ይህንን መሠረታዊ መተከል ከሕዝብ ጀረባ ሊደራደርበት እንደማይችለው ሁሉ፣ ሌላውም ከሕዝብ ጀርባ ለመደራደር ሲሞክርና ለድርድር ሲያቀርባቸው ያስጠነቅቃል/ ለሕዝብም ያጋልጣል። እነኝህን የህዝብ መሠረታዊ የዴሞክራሲ መብቶች ከሕዝብ ጀረባ ለደርደር ሲቀርቡ መከላከል ደግሞ፣ የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የማይገሠሥ መብት ነው። ለምን ቢባል ሕዝብ የሞተባቸውና ካልዘነጋን በስተቀር አሁን በቅርቡ እንኳ በ1997 ዓ.ም ግንቦት ላይ፣ ህዝብ ሬፈረደም ያደረገባቸው ናቸው።  ስለዚህ የህዝባችንን ድምፅና ትግል እኛ ካላከበርነውና ካላስከበረነው ታዲያማ እንደነ ወያኔ  ያሉ ተባዮችና አንባገነኖች፣ እንዲያከበሩት እንጠብቃለን....? ጨረስኩ

የኢሕአፓ አባላት ድርጅታቸውን ለምን ይወዳሉ....? ለምንስ አሁንም እስከመጨረሻው እንታገላለን ብለው በኩራት ቃል ይገባሉ? የሚሉትንና የመሣሰሉትን .....**ይቀጥላል**

የሕዝብ ድምፅ ይከበር! የታሠሩት የፖለቲካ እስረኞኝ በሙሉ ይፈቱ!
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

ቸር እንሡብት
November 25/ 2009